# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## ከሴፕቴምበር 1-10/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ እና

## ከሴፕቴምበር 11-20/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ሴፕቴምበር 2022
አዲስ አበባ

## ርዕስ ገፅ


እ.ኤ.አ ከሴፕተቴምበር 1-10/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ ........ 3
ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10 /2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ........ 4
ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10 /2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት ........ 5
ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10 /2022 ድረስ የነበረው የዝና ብመጠን ........ 6
ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ........ 6
እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1-10/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በእርሻ ሥራ ........ 7
እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........ 7
ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ 7
እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር1-10/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ........ 9
እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........ 9
ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ 9
እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11-20/2022 የሚኖረው የአየር ........ 10
ሁኔታ አዝማሚያ ........ 10
ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከሴፕቴምበር 10-20, 2022 ........ 11
የሚኖረዉ ዝናብ በሚ.ሜ ........ 11
እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11-20/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ 11
እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11-20/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ 12

# እ.ኤ.አ ከሴፕተቴምበር 1-10/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ


ባለፉት አስር ቀናት ለዝናብ መፈጠር መንስኤ የሆኑ የአየር ሁኔታ ገጽታዎች ከሰሜን ምሥራቅና ከምሥራቃዊ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በአንጻራዊ መልኩ የመዳከም ሁኔታ አሣይተዋል። ይሁን እንጂ በየጣልቃዉ ፀሃያማ ሁኔታ እየተስተዋለ፤ የወቅቱ ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ ለተከታታይ ቀናት በብዙ ሥፍራዎች ላይ ዝናብ ሲያገኙ ቆይተዋል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ በፀሃይ ኃይል እየታገዘ ከተፈጠረው ጠንካራ የደመና ክምችት በአንዳንድ በአማራ፣ በምዕራብና በመካከለኛው ኦሮሚያ፣ ቢጋምቤላ፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል እንዲሁም በደቡብ ደጋማ ቦታዎች ላይ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ እንዲኖር አስተዋፅዖ አድርጓል፡፡

በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በአማራ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በምዕራብና መካከለኛዉ ኦሮሚያ፣ ቢጋምቤላ፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ በሲዳማ፣ በደቡብ ደጋማ ሰፍራዎች፣ በደቡብ አፋር፣ በአዲስ አበባ፣ በምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ሀረሪ እና ድሬዳዋን ጨምሮ በብዙ ቦታዎቻቸዉ ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ በብዙ ጣቢዎች ላይ የተመዘገበ ሲሆን፤ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው ስፍራዎች መካከል ለመጥቀስ ያህል በአቦቦ 40.0፣ በበደሌ 42.5፣ በቡኢ 52.4፣ በቦሬ 42.0 እና 48.9፣ በቻግኒ 42.9፣ በድሬዳዋ 40.0፣ በጊኒር 80.0፣ በካቺሴ 45.4፣ በሊሙገነት 88.2፣ በመተሀራ 68.6፣ በናዝሬት 45.4፣ በአማን 54.0፣ በተርጫ 47.4፣ በላሬ 88.0፣ በጉንዶ መስቀል 90.6፣ በፉኙዶ 76.0 እንዲሁም በእንድብር 65.5 በሚ.ሜ የገኙባቸዋል፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በትግራይ፣ በአማራ፣ በቤንሻንጉል-ጉሙዝ፣ ቢጋምቤላ፣ በሲዳማ፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ እና በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልሎች ሁሉም ዞኖች፣ በሁሉም የወለጋና ሸዋ ዞኖች፣ በቡኖ በደሌ፣ በኢሉ አባቦራ፣ በጅማ፣ በአርሲና ምዕራብ አርሲ፣ በምዕራብ ሐረርጌ፣ በአዲስ አበባ፣ በድሬዳዋና ሀረሪ እንዲሁም በሲቲ ዞኖች ላይ ከ25-169 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ4-9 ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፤ በአፋር፣ በፋፈን፣ በምስራቅ ሐረርጌ፣ በባሌ፣ በጉጂና ምዕራብ ጉጂ ዞኖች አንዳንድ ቦታዎች ላይም ከ5-25 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ4 ላነሱ ቀናት ዝናብ ተመዝግቧል (ካርታ 1 እና 2)፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በትግራይ፣ ከአገዋዊ በስተቀር በሁሉም የአማራ ክልል ዞኖች፣ በደቡብ አፋር፣ ቢጋምቤላ ሁሉም ዞኖች፣ በቄለምና ምዕራብ ወለጋ፣ በሆሮ ጉዱሩና ምስራቅ ወለጋ፣ በጅማ፣ በቡኖ በደሌ፣ በምዕራብና ሰሜን ሸዋ(04)፣ በጉጂ፣ በምዕራብ ጉጂና በቦረና አብዛኛዉ ቦታዎች፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ በከፋና ምዕራብ ኦሞ፣ ከሞላ ጎደል በሁሉም የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዘዝቦች ክልል እና ሲዳማ ክልል ዞኖች እንዲሁም ከመተከል ዞን በስተቀር ሁሉም የቤንሻንጉል-ጉሙዝ ዞኖች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ የተመዘገበ ሲሆን፤ በሰሜን አፋር፣ በመተከል ዞን ፣ በባሌ፣ በሲቲና በፋፈን ጥቂት ስፍራዎች ላይ ከመደበኛው ያነሰ የዝናብ መጠን ነበራቸው (ካርታ 3)፡፡


ካርታ 1   እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10 /2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2     እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10 /2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



ካርታ 3   ኢ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10 /2022 ድረስ የነበረው የዝና ብመጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር





ከመደበኛ በታች   መደበኛ   ከመደበኛ በላይ

# እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1-10/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት አሥር ቀናት ለዝናብ መፈጠር አስተዋፅዖ የሚያደርጉ የሚቲዎሮሎጂ ገፅታዎች ከሰሜን ምሥራቅና ከምሥራቃዊ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በአንጻራዊ መልኩ የመዳከም ሁኔታ ቢያሳዩም በተቀሩት በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚና የመኸር አብቃይ በሆኑት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ለተከታታይ ቀናት በብዙ ሥፍራዎች ላይ እርጥበቱ እንደቀጠለና በሂደትም ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ወደሆኑት ወደ ደቡብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ተስፋፍቶ እንደነበረ ከተለያዩ የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች የተሰበሰቡና የተተነተኑ የአግሮ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ይህም ሁኔታ ቀደም ብለው ተዘርተው በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የተለያዩ የረጅም ጊዜ ሰብሎች እንዲሁም ዘግይተው ለተዘሩና በቡቃያና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመካከለኛ ጊዜ ሰብሎች እንዲሁም ለጥራጥሬና ለቅባት እህሎች የተገኘው እርጥበት ገንቢ ሚና ነበረው፡፡ በተጨማሪም ወደ ደቡብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ተስፋፍቶ የነበረው እርጥበት በአካባቢው ለሚገኙ አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለመጠጥ ውኃ አቅርቦትና የዕፅዋት ልምላሜን ከማሻሻል አንፃር ገንቢ ሚና ተጫውቷል፡፡ ይሁን እንጂ ከክረምቱ ዝናብ መጠናከር ጋር ተያይዞ በአንዳንድ በአማራ፣ በቤንሻንጉል-ጉሙዝ፣ በምዕራብና መካከለኛው ኦሮሚያ፣ በጋምቤላ፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል እንዲሁም በደቡብ ደጋማ ቦታዎች ላይ አልፎ አልፎ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት እንደነበረና ይህም ሁኔታ ዝናብ አጠር ለሆኑና ዉሃን የማቆር ሥራዎችን ለመከወን፣ ለግጦሽ ሣር መሻሻልና የመጠጥ ዉሃ አቅርቦት አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ቢሆንም፡፡ በሌላ በኩል ምንም እንኳን የደረሰን ሪፖሪት ባይኖርም በአንዳንድ ስፍራዎች የነበረው ከባድ ዝናብ በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ በሚገኙ ሰብሎች እና ቋሚ ተክሎች ላይ እንዲሁም በመደበኛ ባህሪያቸው በእርጥበት መብዛት በሚታወቁና የመሬት አቀማመጣቸው ተዳፋትና ውሀ ገብ በሆኑ አካባቢዎች ላይ የነበረው የእርጥበት መብዛት አሉታዊ ተጽዕኖ እንደነበረዉ ነው (ካርታ 4) ፡፡


ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ


14
12
10
8
6
4
34
36
38
40
42
44
46
48
እጅግ በጣም እርጥብ
በጣም እርጥብ
እርጥብ
ከፊል ደረቅ
ደረቅ
በጣም ደረቅ

# እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር1-10/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

እ.ኤ.አ 1-10 ሴፕተምበር 2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ በተመለከተ የተሻለ እርጥበት በአብዛኛው የክረምት እርጥበት ተጠቃሚ የአገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ተስተውሏል፡፡ ይህንን ተከትሎ አባይ፣ ባሮአኮቦ፣ ተከዜ ኦሞጊቤ፣ ስምጥሸለቆ፣ የገናሌዳዋ የላይኛውና የመካከለኛው አዋሽ እንዲሁም የላይኛው ዋቢሸበሌ ተፋሰሶች ከፍተኛ እርጥበት አግኝተዋል$ በተጨማሪም በታችኛው አዋሽ፣ በመካከለኛው ገናሌ ዳዋ፣ዋቤ ሸበሌ እንዲሁም አፋር ደናክል ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት ነበራቸው፡፡ በተቀሩት የደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ሁኔታ ስር እንደነበሩ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 5)፡፡

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




# እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11-20/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በሴፕቴምበር ሁለተኛው አሥር ቀናት የክረምት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከሰሜንና ከሰሜን ምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች እየተዳከሙ የሚሄዱበትና ከዚህም ጋር ተያይዞ የወቅቱ ዝናብ በመጠንም ሆነ በሥርጭት በጎላ መልኩ እየቀነሰ በሂደትም የሚያቆምበት ጊዜ ነው፡፡ በሌላ በኩል የክረምት ድንበር (ITCZ) ወደ ምዕራባዊው አጋማሽና ወደ ደቡባዊው የኢትዮጵያ ክፍሎች ስለሚያፈገፍግ ዝናቡ በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ ቀጣይነት የሚኖረው ሲሆን፣ በተመሳሳይ ሁኔታም የደቡብ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ሁለተኛውን የዝናብ ወቅታቸውን ቀስ በቀስ ማግኘት ይጀምራሉ፡፡

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት አሁን ከሚታዩትና በቀጣይነትም ከተተነበዩት የትንበያ መረጃዎች መረዳት እንደተቻለው ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ቀጣይነት ሊኖራቸው እንደሚችልና የክረምቱ ዝናብ በአብዛኛው ወደ ምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚያመዝን ሲሆን፣ በሌላ በኩል የዘንድሮው የክረምት ዝናብ በአንዳንድ በሰሜንና በሰሜን ምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ በአወጣጥ ረገድ ለተወሰኑት ቀናት የመዘግየት አዝማሚያ ሊኖረው ይችላል፡፡

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት <u>ከኦሮሚያ ክልል ሁሉም የወለጋና የሸዋ ዞኖች፣ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ቡኖ በደሌ፣ አርሲ፣ አዲስ አበባ፤ ከአማራ ክልል ምዕራብና ምሥራቅ ጎጃም፣ የሰሜን ጎንደር፣ የባህር ዳር ዙሪያ፣ አዊ ዞን፣ የሰሜን ሸዋ፣ ከትግራይ ክልል የምዕራብና የሰሜን ምዕራብ ዞኖች፣ የቤንሻንጉል ዞኖች፤የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ፤ደቡብ ኦሞ፣ ኮንሶ እና ጌዲዮ በስተቀር መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ እንደሚኖራቸው የሚጠበቅ ሲሆን፣ በተጨማሪም ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከባድ ዝናብ ሊኖር ይችላል፡፡ በተጨማሪም የሲዳማ እና የጋምቤላ ዞኖች፤ የደቡብ ጎንደር፣ የሰሜንና የደቡብ ወሎ ዞኖች፣ የዋግ ህምራ፣ የደቡብ፣ የመካከለኛዉና የምሥራቅ ትግራይ ዞኖች፤ የአፋር ዞን 3 እና 5፤ ምዕራብና ምሥራቅ ሐረርጌ፤ ባሌ፣ ጉጂ፤ ድሬዳዋና ሐረሪ ፤የደቡብ ኦሞ፣ የሰገን ህዝቦች፣ የምዕራብ ኦሞ፤ እንዲሁም የፋፈንና የሲቲ ዞኖች በአንዳንድ ሥፍራዎቻቸው ላይ በአብዛኛው ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል። የተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች በአብዛኛው ደረቅ ሆነው ይሰነብታሉ።</u>




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከሴፕቴምበር 10-20, 2022
የሚኖረዉ ዝናብ በሚ.ሜ

## እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11-20/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ በሴፕቴምበር ሁለተኛው አሥር ቀናት የእርጥበት ሁኔታው ከሰሜንና ከሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች እቀነሰ እንደሚሄድና በሂደትም የሚያቆምበት ነው፡፡ ቀደም ብለው የተዘሩ ሰብሎች በአብዛኛው ፍሬ በመሙላት ወደ መብሰል የሚደርሱበትና በአንዳንድ ክረምቱ ቀድሞ በሚወጣባቸው አካባቢዎችም የሰብል ስብሰባ ሊካሄድ የሚችልበትም ጊዜ ነው፡፡ በሌላ አንፃር ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ለሆኑት የደቡብ የሀገሪቱ አካባቢዎች የግብርና ስራ እንቅስቃሴ የሚጀምሩበት ወቅት ሲሆን፣ በሂደትም የአረንጓዴ እፅዋት ስርጭትና የግጦሽ ሳር ልምላሜ ቀስ በቀስ እየጨመረ የሚሄድበትም ጊዜ ነው፡፡

በሚቀጥለው የሴፕቴምበር ሁለተኛው አስር ቀናት የእርጥበት ሁኔታው አሁን እየታየ ባለው መልክ ቀጣይነት ሊኖረው እንደሚችልና በአብዛኛው ወደ ምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እንደሚያተኩር የሚጠበቅ ሲሆን፣ ይህም ሁኔታ እየተካሄደ ላለው አጠቃላይ የግብርናው ዘርፍ ገንቢ ሚና ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም ቀደም ብለው ለተዘሩና ፍሬ በመያዝ ላይ ለሚገኙ፣ ዘግይተው ለተዘሩና በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ ላሉ ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች የተሟላ እድገት የሚያስፈልጋቸውን

የውኃ አቅርቦት ከማረጋገጥ አንፃር አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል፡፡ እንዲሁም የዘንድሮው የክረምት ዝናብ በአንዳንድ በሰሜንና በሰሜን ምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ በአወጣጥ ረገድ ለተወሰኑ ቀናት የመዘግየት አዝማሚያ በመኖሩ በአንዳንድ አካባቢዎች ዘግይተው ለተዘሩና እድገታቸውን ላልጨረሱ የመኸር ሰብሎች አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል ፡፡ በተጨማሪም በመጠን ረገድ አነስተኛ ቢሆንም፤ ወደ ደቡብ የሚያደርገው መስፋፋት ለአርብቶ አደርና ለከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች በጎ ሚና ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም ውኃ አጠር የሆኑ አካባቢዎች የሚገኘውን የዝናብ ውኃ ለመሰብሰብና ለማከማችት መልካም አጋጣሚ ስለሚያገኙ ይህንኑ ለማከናወን የሚያስችል ዝግጅት እንዲያደርጉ ይመከራሉ፡፡ እንዲሁም ከመደበኛ በላይ ዝናብ እንደሚያገኙና አልፎ አልፎም ከባድ ዝናብ ሊኖራቸው እንደሚችል በትንበያው በተጠቀሱት አካባቢዎች አስቀድሞ ልዩ ትኩረትና ጥንቃቄ እንዲደረግ የሚመከር ሲሆን፤ በተለይም አንዳንድ ቦታዎች ከባድ ዝናብ ከመኖሩ ጋር ተያይዞ እርጥበቱ ከመጠን በላይ ስለሚሆን በዚህም ምክንያት ውሃ ማሳ ላይ እንዳይተኛ ቦይ በማውጣትና የማንጣፈፍ ስራ መስራትና ነባር የሆኑ ቦዮችን ከተለያዩ የውኃ ፍሰትን ከሚከለክሉ ነገሮች ማፅዳት ያስፈልጋል፡፡ በሌላ በኩል በአንዳንድ አካባቢዎች ሰብሎች እየደረሱ ከመሄዳቸው ጋር ተያይዞ የሰብል ስብሰባ እየተከናወነ ሲሆን፤ የሚጠበቀው እርጥበት ጉዳት እንዳያደርስ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ያሰፈልጋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11-20/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት ሴፕተምበር ሁለተኛ አስር ቀናት በአብዛኛው በመካከለኛው፣ በደቡብና በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍል የሚገኙት ተፋሰሶች ላይ የተሻለ እርጥበት ሊኖራቸው እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ያመለክታል፡፡ ይህንን ተከትሎ በአብዛኛው አባይ፣ የላይኛውና የመካከለኛው ባሮአኮቦ፣ ኦሞጊቤ፣ ስምጥሸለቆ፣ የላይኛው አዋሽ፣ ተከዜ፣ ዋቢሸበሌ እንዲሁም የገናሌዳዋ ተፋሰሶች ላይ ከከፍተኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ የእርጥበት መጠን እንደሚያገኙ ይጠበቃል። ከሚኖረው ከፍተኛ እርጥበት በተጠቀሱት ተፋሰሶች ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ ቦታዎቻቸው ላይ ጥንቃቄና ክትትል ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም በአብዛኛው አዋሽ፣ ተከዜ፣ መካከለኛው ገናሌዳዋ፣ የታችኛው ስምጥሸለቆ እና ኦሞጊቤ የመካከለኛው ዋቢሸበሌ ተፋሰሶች መጠነኛ የእርጥበት መጠን እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡ የተቀሩት ተፋሰሶች በአብዛኛው ቦታዎቻቸው ላይ ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ሆነው እንደሚቆዩ ይጠበቃል፡፡